chilot.wordpress.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፫ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

16th Year No. 24
ADDIS ABABA May 21st 2010

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፸፯/፪ሺ፪
የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ገጽ ፭ሺ፪፻፷

CONTENTS

Regulation No.177/2010
Information Technology Park Corporation Establishment Council of Ministers Regulation ...... Page 5260

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፸፯/፪ሺ፪
### የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፸፯/፪ሺ፪» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. መቋቋም

፩. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪. ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

፭. ዓላማ

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፦

፩. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ማልማትና ማካሄድ፤ እና

፪. ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን መስጠት።

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

### Council of Ministers Regulation No. 177/2010
### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE INFORMATION TECHNOLOGY PARK CORPORATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. ***Short Title***

This Regulation may be cited as the "Information Technology Park Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 177/2010".

2. ***Establishment***

1/ The Information Technology Park Corporation (hereinafter the "Corporation") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Corporation shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 177/1992.

3. ***Supervising Authority***

The Ethiopian Information and Communication Technology Development Agency shall be the supervising authority of the Corporation.

4. ***Head Office***

The Corporation shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. ***Purpose***

The purposes for which the Corporation is established are:

1. to develop and operate information technology park; and
2. to render services related to information technology park.

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

